<u>*እኔና የጀርመኑ ኢምባሲ የሥራ ማስታወቂያ*</u>

*በኢትዮጲያ የጀርመን ኢምባሲ ባወጣው ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ ጋር ተያይዞ ለአምባሳደሩ በኢሜል ያቀረብኩት ጥያቄ ይሄው እስካሁን ድረስ እረፍት እንደነሳኝ አለ። ልረሳው ብሞክርም በሄድኩበት ይከተለኛል። በተለይ ማህበራዊ ድረገፆች ላይ በማደርጋቸው ውይይቶች ሁሉ ጣልቃ እየገባ ይበጠብጠኛል። ለአምስት ቀናት ብቻ የሚያውቁኝ ሆኑ ከአምስት አመት በላይ የሚያውቁኝ ጓደኞቼ ሁሉም በአንድነት በጥላቻ ከሰውኛል፣ "ዘረኛ" በሚል ወንጅለውኛል። በአካል ያጋጠመኝ ነገር የለም። ሆኖም ግን፣ በማህበራዊ ድረገፆች፣ በኢሜልና በስልክ ቅጥ-ያጣ ስድብ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ደርሶኛል። በማህበራዊ ድረገፆች ከተለመደው ወጣ ያሉ ሃሳቦችና አስተያየቶች ስለምሰጥ ለእንደዚህ ያሉ ምላሾች ብዙም ትኩረት አልሰጥም ነበር። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በተከታታይ የማወጣቸውን ፅሁፎች ለማንበብ፣ በዚህም የእኔን የግል እምነትና አመለካከት ለማወቅ እድል የሌላቸው ናቸው። ባለፉት 6 ወራት ብቻ ያወጣኋቸውን 37 ፅሁፎች አንድ-በአንድ እያነበበ ኢዲት ሲያደርግ የነበረ ኢዲተር ግን እንኳን የአንድን ፅሁፍ አውድ ይቅርና ውስጣዊ አስተሳሰቤን የሚያውቅ ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን፣ እሱም እንደሌሎች በዚህ ጉዳይ ላይ ጥርጣሬ ሲያድርበት ሳይ ነገሩ ከእሳቤዬ ውጪ እንደሆነ ተሰማኝ።*

*በትላንትናው እለት ደግሞ አንድ ሌላ ግለሰብ በኢሜል ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንድሰጠው ጠየቀኝ። "ይኄው እስካሁን ድረስ ግራ እንደተጋባሁ አለሁ... ጥፋቴ ምኑ ላይ እንደሆነ እንኳን ማወቅ አልቻልኩም" ከሚል ማስታወሻ ጋር ለአምባሳደሩ የፃፍለኩትን ኢሜል ለእሱም ላኩለት። ፍፁም ባልጠበቅኩት መልኩ እሱም "ያንን ጥያቄ በመጠየቄ "የሰራህው ስህተት እንዴት እስካሁን ድረስ አልገባህም" በሚል ተናደደብኝ። እውነቱ ግን ይሄ ነው። በእርግጥ ሳላውቅ ያጠፋሁት ጥፋት ካለ በይፋ ይቅርታ ለመጠይቅ ዝግጁ ነኝ። ነገር ግን፣ አሁንም ቢሆን ጥፋቴ፥ የሰራሁት ስህተት አልገባኝም። ስለዚህ፣ ከታች እንደምትመለከቱት ኢምባሲው ያወጣው ክፍት የሥራ-ማስታወቂያ፣ ለአምባሳደሩ የፃፍኩት ኢሜልና የተሰጠኝ ምላሽን አንድ ላይ በማጠናቀር ሃሳቤን በቅንነት ለማስረዳት እሞክራለሁ። እናንተም ያላችሁን አስተያየት በዚህ መድረክና በሌሎች ድረገፆች፣ እንዲሁም በግል የመልዕክት አድራሻዬ እንድታሳውቁኝ በቅድሚያ እለምናችኋለሁ።*

*የችግሩ መንስዔ በኢትዮጲያ የጀርመን ኢምባሲ ግንቦት 04/2016 (እ.አ.አ) ያወጣው ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ነው። እኔ በግሌ ማስታወቂያውን ያየሁት ከአንድ ሳምንታ በኋላ ሲሆን፣ ለአምባሳደሩ ያቀረብኩት ጥያቄና የተሰጠኝ ምላሽ እንደሚከተለው በቅደም-ተከተል ተቀምጧል።*



attachment(2).pdf

Embassy
of the Federal Republic of Germany
Addis Ababa

Addis Ababa, 04. May 2016

**Job Vacancy**

The Embassy of the Federal Republic of Germany invites for applications for the following job vacancy available from middle of June 2016:

**Assistant Clerk at the Visa- and Consular Section**

**Job description:**
- Acceptance of visa applications
- Processing of visa applications
- Providing information about visa matters in writing as well as verbally
- Acceptance and accounting of visa fees
- Management of filing system

**Requirements:**
- **Good knowledge of Tigrinya is a precondition for any aplication!**
- Preferably completed university degree
- Very good computer skills of all current programmes
- Very good communicating and analytical skills- ability to work in a team
- Experience in administrative services would be an advantage

**Language skills:**
- Fluent in **German** and **English** with good writing skills
- Fluent in **Tigrinya** and **Amharic**

The salary will be appropriate and customary, the contract is based on Ethiopian law.

**Please submit your complete application including the following documents:**
- curriculum vitae with a recent photograph
- letters of recommendation as well as school certificates (copy)
- proof of university degree (copy)
- proof of previous employment (copy)



Demanding explanation on your employment practices Inbox

Seyoum Teshome
to info, Vw-S1
May 12 View details

Dear Ambassador Schmidt, J.

Your honour, greetings. My name is Seyoum Teshome, a lecturer at Ambo University and a freelance blogger at ethiothinkthank.com and hornaffars.com. Am writing this email looking for an explanation with regard to the vacancy announcement posted by your Embassy on 04. May 2016 (Please see the attachment). It went viral on social media, particularly on Facebook. Am wondering why an "Assistant Clerk at the Visa- and Consular Section" of your Embassy must speak "Tigrinya" language but not Oromiffa, Guragegn, Wolayitagn.... etc. How is it possible for a language which merely spoken by 5% of the Ethiopian population is a precondition? Such constriction on the rest 95% certainly amounts to discrimination, which is against the democratic values and employment policies of the Federal Republic of Germany.

With regards,

Seyoum T

.ADDI PR-1 Hanna, Benja...
to me
May 13 View details

Dear Ato Seyoum,

Thank you for your interest in the German Embassy. Ambassador Schmidt asked me to respond to your mail on his behalf. The specific requirements needed for this particular position of an Assistant Clerk at the Visa- and Consular Section follow internal management considerations. As a matter of principle, the German Embassy does not to comment on internal management considerations.

Thank you for your understanding.

Regards,
Benjamin Hanna

*ስዩም ተሾመ፣ አምቦ ዩኒቨርሲቲ ወሊሶ ካምፓስ፣ ወሊሶ*
*Email: seyee123@gmail.com Blogs: http://ethiothinkthank.com እና http://hornaffairs.com/am/author/seyoumteshome/*

*ከላይ በምስሉ ላይ እንደምትመለከቱት ለሥራ ቦታው አስፈላጊ የሆኑ ቋንቋዎች "የቋንቋ ክህሎት" (Language Skills) በሚለው መስፈርት ስር ተዘርዝረዋል። ስለዚህ፣ በክፍት የሥራ ቦታው መወዳደር የሚሻ ማንኛውም ግለሰብ ከአራቱ ቋንቋዎች አንዱን አቀላጥፎ መናገር የማይችል ከሆነ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟላም ማለት ነው። የትግርኛ ቋንቋ ለሥራ ቦታው በተለየ አስፈላጊ እንደሆነ ለማሳወቅ ከተፈለገ ደግሞ "የቋንቋ ክህሎት" በሚለው ስር የተቀመተው መስፈርት በቂ ነው። የትግርኛ ቋንቋን አቀላጥፎ ከመናገር በዘለለ፣ በትግሪኛ ቋንቋ ላይ የላቀ ዕውቀት ያለው ሰራተኛ ተፈልጎ ከሆነ፣ ልክ በጀርመንኛና እንግሊዘኛ ስር "Fluent in German and English with good writing skills" በሚል እንደተጠቀሰው ሁሉ፣ ለትግሪኛም "Fluent in Tigrinya with a good knowledge" በማለት ወይም በሌላ መልኩ ማስቀመጥ ይቻል ነበር። የተደረገው ነገር ግን ሌላ ነው። በሥራ ቦታው ላይ የትግሪኛ ቋንቋ እንደ መስፈርት ሳይሆን እንደ "ቅድመ-ሁኔታ" (precondition) ተቀምጧል። በምስሉ ላይ እንደሚታየው፣ ጉዳዩ የተለየ ትኩረት እንዲሰጠው በማለት በቀይ ቀለም ተፅፎ ቃለ-አጋኖ ተደርጎበታል።*

*ይህን የሥራ ማስታወቂያ ለእኔ የደረሰኝ በመጀመሪያ ደረኩት ነገር የመረጃውን ትክክለኘነት ማጣራት ነው። ትክክለኘነቱን ካረጋገጥኩ በኋላ ደግሞ በኢትዮጲያ የጀርመን አምባሳደር ለሆኑት ሚ/ር "Schmidt" ደብዳቤ ፅፎ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡኝ መጠየቅ ነው። ምክንያቱም ቋንቋ ከመግባቢያነት አልፎ እንደ ልዩ የሙያ ዕውቀት ወይም የመለያ መስፈርት በክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ላይ ቅድመ-ሁኔታ ተደርጎ ስመለከት፣ ቋንቋው ትግሪኛ ሆነ አማርኛ፣ ጀርመንኛ ሆነ እንግሊዘኛ፣ ኦሮምኛ፥ አፋርኛ፥ ሶማሊኛ፥ ሲዳምኛ፥ አገውኛ፥ .... ወዘተ፣ ግዜው መቼም ይሁን መቼ፣ ቦታውም የትም ይሁን የት፣... ልክ ባለፈው እንዳደረኩት "ማብራሪያ ይሰጠኝ" ብዬ በይፋ እጠይቃለሁ። ይህ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ከወጣ ከአንድ ሳምንት በኋላ ግንቦት 12/2016 (እ.አ.አ)ለጀርመኑ አምባሳደር ኢሜል ፅፌ፣ በማግስቱ በፀኃፊያቸው በኩል ምላሽ ተሰጠኝ። ለጀርመኑ አምባሳደር ያቀረብኩት ጥያቄ ትክክለኛና አግባብ የሆነ መልስ አለው የሚል እምነት ነበረኝ። ምንም እንኳን ምላሽ መስጠት የሚጠበቅበት የጀርመን ኢምባሲ ቢሆንም፣ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተል የአንድ ጋዜጣ አዘጋጅ ለጥያቄዬ መልሱን ከጥሩ ማብራሪያ ጋር ሰጥቶኛል። ነገር ግን፣ ለእኔ ቁም-ነገሩ፣ በምላሹ በቂ ማብራሪያ ማግኘቴ ወይም ያለማግኘቴ አይደለም። ከዚያ ይልቅ፣ ጥያቄውን በቀጥታ ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ምላሽ እንዲሰጥበት ማድረግ ነው። በዚህም፣ በጉዳዩ ዙሪያ ያለውን ግራ መጋባትና የተፈጠረውን የተዛባ አመለካከት ለመቅረፍ የራስን አስተዋፅዖ አበርክቼያለሁ።*

*በአጠቃላይ፣ የጀርመን ኢምባሲ ካወጣው ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ጋር በተያያዘ ያስተዋልኳቸው ሦስት ችግሮች ናቸው። አንደኛ፡- መደበኛ የማስታወቂያ አፃፃፍ ስልትን ያልተከተለ መሆኑ፣ እንዲሁም አላስፈላጊ የቃላት አጠቃቀምና የፊደላት ግድፈት (ለምሳሌ፡-"Apllication!") ያለበት መሆኑ መልዕክቱን በተገቢው ሁኔታ እንዳያስተላልፍ አድርጎታል። በመሆኑም፣ የማስታወቂያው መልዕክት በተሳሳተ መልኩ እንዲተረጎምና የተዛባ አመለካከት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ሁለተኛ፡- የጀርመን ኢምባሲ "የውስጥ አሰራር ነው" በሚል መርህ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ማብራሪያ ለመስጠት ፍቃደኛ አልነበረም። የውስጥ አሰራር ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ በቋንቋ መስፈርት ስር ከተቀመጡት አራት ቋንቋዎች ውስጥ የትግሪኛ ቋንቋ ለዚያ የሥራ ቦታ በተለየ መልኩ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ማብራሪያ እንዳይሰጥ የሚደርገው ነገር አልነበረም። ይህ ቢሆን ኖሮ በጉዳዩ ዙሪያ የተፈጠረውን ውዥንብር ማስወገድ ይቻል ነበር። ሦስተኛ፡- የሀገራችን የፖለቲካ ሊሂቃን በእንደዚህ ያሉ ጉዳዮች ላይ ከተገቢው አካል ማብራሪያ በመጠየቅ፣ በማህብረሰቡ ውስጥ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ ግንዛቤ ለማስረፅ ጥረት ያለማድረጋቸው ነው። እንዲህ ያለ፣ የተሳሳተ ግንዛቤና የተዛባ አመለካከት ሊፈጥር የሚችል ነገርን "ለምንና እንዴት?" ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ በማህበራዊ ድረገፆች ላይ እየተቀባበሉ ቂምና ጥላቻን ማራገብ ነበር የመረጡት። ጉዳዩን ለማጣራት ጥረት ማድረግ በራሱ እንደ ጥፋት ተወስዶ በተለያየ መልኩ ጫናና ተፅዕኖ ሲደረግ እንደነበር በእኔ ላይ የደረሰውን ብቻ ማሳያ ነው።*

*ከላይ በሦስተኘነት የተጠቀሰው ችግር፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በሀገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ላይ የሚስተዋል ችግር ነው። በሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በተለያይ መድረኮች የሚደረጉ ውይይቶች ፅንፈኛ አቋም በሚያራምዱ ግለሰቦች ቁጥጥር ስር ወድቋል። በትክክለኛ መራጃና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ውይይት ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የለም። ይህ ዛሬ ላይ የተገለጠልኝ እውነት ሳይሆን በተለያዩ ድረገፆች ላይ ተከታታይ ፅሁፎች እንድፅፍ ያደረገኝ መሰረታዊ ምክንያት ነው። ለምሳሌ፣ በወቅቱ "አብዛኞቹ የሀገሪቱ የፖለቲካ ልሂቃን በጉዳዩ ላይ በሰጡት አስተያየት የሚያንፀባርቁት ሃሳብ ምን ይመስላል?" ብሎ ለመዳሰስ የሞከረ ሰው ምን እያልኩ እንደሆነ ይገነዘባል። ምክንያቱም፣ በአብዛኞቹ ልሂቃን ሲሉት የነበረው ነገር፤ "ድሮስ የወያኔ ፖለቲካ፣... ሁሉንም ቦታ እነሱ የተቆጣጠሩት እንግዲህ፣.... ዉጪ ጉዳይ ብትሄድ ደግሞ ጉድ ታያለህ...." የሚል፣ ቆይቶ በሚፈነዳ ቂምና ጥላቻ የታጨቁ ስሜት ሲያንፀባርቁ ነበር። እንዲህ ያለ ጥላቻና ቂም እንኳን አብሬው በኖርኩት የትግራይ ማህበረሰብ ላይ ቀርቶ፣ "መቼም - የትም - በማንም ላይ ቢሆን ይህ እንዲሆን አልፈቅድም።*

*በመጠየቅ እውነት ይገኛል፣ ባለመጠየቅ ግን ጥርጣሬና አለመተማመን ይሰፍናል። ከዚህ ደግሞ ጭፍን ጥላቻና ዘረኘነት ይወለዳል። ይኼ የእኔ የግል ስብዕናና የሕይወት መርህ ነው። እኔ ደግሞ፣ ከልጅነቴ ጀምሮ "ይሄ ነገር እንዴትና ለምን እንዲህ ሆነ?" ብዬ ከመጠየቅ ወደኋላ ብዬ አላውቅም። አስታውሳለሁ፣ የ14 ዓመት ልጅ እያለሁ በሆነ ጉዳይ ላይ እየተከራከርን ሳለ ድንገት በመሃል አመለጠኝና አባቴን መልስ የሌለው ጥያቄ ጠየኩት። ድንገት "እስኪ ከቻልክ በእግዚያብሄር እና በእየሱስ ክርስቶስ መካከል ያለውን ልዩነት ንገረኝ?" ስል ጠየኩት። በወቅቱ አባቴ በጣም ተቆጣ! ከፊቱ እንድጠፋለት በግልምጫው አባረረኝ። ምን እንዳስቆጣው የገባኝ ግን ከብዙ አመታት በኋላ ነው። ለካስ አባቴ በእምነት ብቻ የተቀበለውን እውነት በምክንያት እንዲያስረዳኝ ነበር የጠየቅኩት። ስለዚህ፣ ምክንያታዊነት መርህ በዝርዝር ሊያስረዳኝ የማይቻለውን ጥያቄ በመጠየቄ ተበሳጨ፥ ተቆጣ፣ እኔም ያንን ጥያቄ መልሼ አላነሳሁበትም። እርግጥ ነው፣ ቁጣና ብስጭት ለጥያቄ መልስ የሚሆኑት በእውቀት ላይ የተመሰረተ ምላሽ መስጠት ሲሳነን ነው።*

*በፅሁፎቼ የማውቀውን በማካፈልና ከዚያም ከማገኘው የሞራል እርካታ በዘለለ አንድም ቀን የተለየ ጥቅም አግኝቼ አላውቅም። በተከታታይ ለማወጣቸው ፅሁፎች ክፍያ ጠይቄም ሆነ ተቀብዬ አላውቅም። እኔ በተለያዩ ድረገፆች ላይ ረጃጅምና ተከታታይ ፅሁፎችን መፃፍ የጀመርኩት ለግል ጥቅም ሳይሆን የማህብረሰቡ ግንዛቤ ለማዳበር የበኩሌን አስተዋፅዖ አበረክታለሁ በሚል እምነት ነው። ለዚህ ደግሞ "በተሳሳተ መረጃ ላይ*

የተመሰረተ የተዛባ አመለካከትን፣ ጭፍን ጥላቻና ዘረኝነት እታገላለሁ" የሚል መርህ ይዤ ነው የተነሳሁት። ይሄ ድንገት ዛሬ ላይ የተገለጠልኝ እውነት ሳይሆን ገና መፃፍ ስጀምር የነበረኝ አቋም ነው። ለዚህ ደግሞ የመጀመሪያዬን ፅሁፍ aigaforum ላይ ሳወጣ የሚከተለውን ጥያቄ በማንሳት ነበር፡-

> " *Of course, one cannot evade anti-conceptual arguments altogether as they are the reflections of a low level of comprehension on the subject. And this is archetypal to all underdeveloped nations where social and political problems are barely scrutinized in their entirety. …The political sphere is filled with men whose unthinking loyalty to their belief is what held the whole creaky system together. By and large, the nation's politics is often framed by thugs who conventionally play the zero-sum blame game, alleging somebody but not themselves. They do hate mongering as a full time job, and spent the rest of their time praying for err of the other group for them to say 'I told you so,' which is the only way to authenticate their position. It seems idiosyncratic to Ethiopians that we are all thin-skinned to discuss political issues objectively. In the intellectual sphere, we don't make a sober assessment on the erroneous assumptions concerning the socioeconomic and political structure of the nation. … Intellectuals also failed to boldly criticize the programs and/or scrutinize the activities of local political groups which makes them liable for the prevalence of the current 'catch-22 politics' in Ethiopia.*

ለጀርመን ኢምባሲ የፃፍኩትን ኢሜል መሰረት በማድረግ እኔን ዘረኛና ለትግራይ ህዝብ ጥላቻ እንዳለኝ አድርጎ ማሰብ ፍፁም ስህተት ነው። በእርግጥ ጥያቄዉን መጠየቄ ስህተት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፣ በግምት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳልይዝ አድርጎኛልና። ከዚህ በተረፈ፣ የአንድን ፅሁፍ ሃሳብ በጭብጡ ሊመዘን ይችል ይሆናል። በአንድና ሁለት ፅሁፍ ግን የፀኃፊውን ሃሳብ፣ አስተሳሰብና አመለካከት ለመመዘን ይከብዳል። ምክንያቱም፣ አንድ ፅሁፍ የራሱ የሆነ ሃሳብ ሊኖረው ይችላል፣ ፅኃፊው ግን ሃሳብ ብቻ ሳይሆን አስተሳሰብ ነው ያለው። በአንድ ፅሁፍ መልዕክት የፀኃፊውን አመለካከት መመዘን ስህተት ነው። በመሆኑም፣ በተለያየ አጋጣሚ፣ በማህበራዊ ድረገፆች ላይ ካወጣኋቸው ፅሁፎች ውስጥ የተወሰኑትን በመምረጥ ያለምንም ለውጥ እንደወረዱ አቅርቢያቸዋለሁ። እነዚህንና ሌሎች ፅሁፎቼን ካነበባችሁ በኋላ አሁንም ዘረኛና ጥላቻ አለብህ የምትሉኝ ከሆነ፣ ድፍረት አይሁንብኝና፣ "ዘረኛ" ያላችሁት እኔን ሳይሆን እራሳችሁን እንደሆነ አስቤ እተወዋለሁ።

### July 20, 2015: "የትግሬን" ኢትዮጲያዊነት ከምትጠራጠር የታሪክ ዕውቀትህን ተጠራጠር!!!

ለውድ Ramathora Dertogada
ስምሽን በአማርኛ ለመፃፍ ሞክሬ ከበደኝና ተውኩት…
"ትግርኛና ኢትዮጲያዊነት" በሚል ስለ ትግሬ ኢትዮጲያዊነት መልመጃ ልትሰጪን እየሞከርሽ ነው። ሙከራሽ ችግር የለውም። ነገር ግን፣ የሃይማኖትና የመንግስታዊ ስርዓቱ እምብርት የሆነውን ትግራይ፣ የኢትዮጲያዊነት እትብት የተቀበረበትን ማህበረሰብ "ኢትዮጲያዊ" ስለመሆኑ መልመጃ ለመስጠት መሞከር ትርፉ ድካም ነው። ከዚያ ይልቅ፣ "ይህን ንፁህ ኢትዮጲያዊ ህዝብ "ባንዳ"ብለው ያለ ስሙ ስም የተሰጠበት ምክንያት ምንድነው?" ብሎ መጠየቅ ስለጉዳዩ የተሻለ ግንዛቤ ያስገኛል። ፕ/ር መስፍን፤ "ያለ ትግራይ፣ የኢትዮጲያ ታሪክ መግቢያ የሌለው መፅሃፍ ነው" ባለ አንደበቱ "የትግሬ ህዝብ እንደ ፋብሪካ ሳሙና አንድ ዓይነት…(ሙሉ ዓ.ነገሩን አላስታውስም)" ብሏል። የመጀመሪያው ምሁራዊ አስተያየት ሲሆን ሁለተኛው ዓ.ነገር ግን ለፖለቲካዊ ፍጆታ የተሰጠ ነው። እንግዲህ፣ ጥሬን ከብስሉ እየለዩ መውሰድ እንጂ የማንም ግባሶ "ባንዳ" ምናምን እያለ በቀባጠረ ቁጥር መልመጃ ለመስጠት መነሳት ፋይዳ ቢስ ነው።

### July 20 2015: ዘረኝነት = ድንቁርና - ብሔር

አበበ ገላውን "በጭፍን ጥላቻ የታጨቀ ግብዝ ዘረኛ" ስል "አ…ሹ!" ስትሉ የነበራችሁ ሰዎች፣ ዘርዓይ ሀይለማሪያምን በተመሣሣይ ስገልፀው "አ…ይ!" ያላችሁ ወዳጆቼ፤ በእኔ እና በእናንተ መካከል ልዩነት አለ። ለእኔ የዘረኝነት መንስዔው #ድንቁርና ነው። ለእናንተ የዘረኝነት መንስዔው #ብሔር ነው!!!
የውሾን ስም የጠራ ውሾ ነው።

### Sep 7, 2015: ትንሽ ስለ ብሔር ፖለቲካ

"አማራ፣ ወይም አማርኛን አቀላጥፎ የሚናገር (aka አማራናይዝድ) በመሆኔ ተጠቃሚ አይደለሁም" የሚል ካለ ውሸታም ነው። ለምን ቢባል፣ በአዲስ አበባና የፌድራል መስሪያ ቤቶች ለመቀጠር የቋንቋ ችግር አልገጠመውም፣ እንዲሁም ስምን እስከመቀየር በሚያደርስ የማንነት ቀውስ (Identity Crisis) ውስጥ አልገባም።

### Dec 5, 2015

ማንኛውም ውይይት፤ "አማራ ነው…ኦሮሞ? ትግሬ…ሐደሬ? ወይስ ጉራጌ?" ተብሎ ተጠይቆና ተፈርጆ በሚጀመርበት ሀገር፣ እውነተኛ ሃሳብ ተነግሮ'ም፣ ተሰምቶ'ም አይታወቅ። እንዲህ በመምሰልና ማስመሰል የተጀቦነ ሃሳብ ዘወትር ሲደጋገም አስተሳሰባችን ይሆናል። እንዲህ ከምክንያታዊ ግንዛቤ በፀዳ መልኩ በአሉባልታ ላይ የተገነባን አመለካከት ይዘን አደባባይ ስንወጣ ደግሞ ት…ን…ሽ እንኳን አናፍርም? እንደው ግን ለመሆኑ፣ በምክንያታዊ አስተሳሰብ የሚመራ ፍጡር እንዴት እንደ እንስሳ ማንነቱ በመንጋው ምንነት ይወሰናል???

### July 29 2015: ለኢህአዴግ የህዝብ ግንኙነት ክፍል

ጉዳዩ፡- የፓርቲው የውስጥ ጠላቶችን ስለማሳወቅ
ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው፣ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ማህበራዊ ድህረ ገፆች፣ በተለይ ፌስቡክ (Facebook)፣ ንቁ የሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚደረግበት መድረክ እየሆነ እንደመጣ ግልፅ ነው። በዚህ ሚድያ አማካኝነት ገዢው ፓርቲ ለሚያከናውናቸው የተለያዩ ተግባራት አፈፃፀም ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦች በትችት መልክ እንደሚነሱ ይታወቃል። ሆኖም ግን፣ የፓርቲው ደጋፊዎች/አባላት ነን የሚሉ አንዳንድ ግለሰቦች፤
1ኛ፡- በተጠቀሰው ሚድያ ሃሳብ በነፃ እንዳይሸረሸር፣ እንዲሁም ሃሳቡ በውይይትና ክርክር ዳብሮ ለፓርቲው ከፍተኛ ሥራ-አስፈፃሚዎች እንዳይደርሱ እንቅፋት በመሆን፣
2ኛ፡- እነሱ ከሚያውቁት ውጪ ለየትና ወጣ ያለ ሃሳብ ሲቀርብ በስድብ፣ ጥላቻና ዛቻ የታጨቁ አስተያየቶችን በመሰንዘር ለፓርቲው አሰራር ገንቢና ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦች በድህረ-ገፁ እንዳይቀርቡ ማነቆ በመሆን፣ ለፓርቲው የህዝብ ግንኙት ሥራ ተግዳሮት ሆነዋል። በመሆኑም፣ የተጠቀሱት የፓርቲው ደጋፊዎች/አባላት ባለማወቅ የፓርቲውን መልካም ስም ጥላሸት ከሚቀባ ተግባር እንዲታቀቡ መመሪያ ሊሰጣቸውና አስፈላጊው የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ አሳስባለሁ። በመጨረሻም፣ በተጠቀሰው ተግባር የተሰማሩ ግለሰቦችን ስም ዝርዝር ከፌስቡክ ተጠቃሚዎች በአስተያየት (Comment) መልክ በመሰብሰብ መረጃውን አጠናቅረን የምንልክ መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ።

*ከሠላምታ ጋር*
*ሰዩም ተ.*

## [Sep 19 ,2015]

*ህወሃትን እና የትግራይ ህዝብን መቀላቀል ፍፁም ስህተት ነው። ነገር ግን መሰረታዊ ጥያቄ መሆን ያለበት፤ "እንዴት ሰው ህዝብን ከገዢ መደብ መለየት ይሳነዋል?" የሚለው ሳይሆን "ይሄ ብሔርን ከገዢ መደብ ቀላቅሎ የሚወቃ ግርድፍ የፖለቲካ አመለካከት እንዴት መጣ?" የሚለው ነው። በዋናነት ይህ የፖለቲካ አመለካከት #በዋለልኝ ተፀንሶ፣ #በመለስ_ዜናዊ የተወለደ ነው። የአማራን ብሔር ከፊውዳሉ የገዢ መደብ ጋር ቀላቅሎ በመውቀስ የተጀመረ ስርዓት መጨረሻው የትግራይ ህዝብን ከህወሃት ጋር መቀላቀል ሆነ። በአንድ በኩል አማራ የተባለን ሁሉ "ትምክተኛ እና የቀድሞ ስርዓት ናፋቂ" በሚል እያንጓጠጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ "የትግራይ ህዝብ ከህውሃት ተለየ ነው" ብሎ ማለት ፋይዳ የለውም። ይልቅስ መለወጥ ካለበት በዛሬይቱ ኢትዮጲያ የተንሰራፋውን #በብሔርተኝነት_የጦዘ ፖለቲካዊ ስረዓት ነው። ይህ እንዲሆን ሌላ ዋለልኝ፣ ሌላ አብዮት ያስፈልግናል!!!*

## [Oct 12, 2015: በጠብታ ውሃ ውስጥ ጉማሬ አየን" የሚሉ አይታሰሩ...]

*ከላይ የተጠቀሰው አባባል የተለየ ቅጥፈት ወይም የተጋነነ ውሸትን ለመግለፅ የሚውልና የጋዜጠኞችን የስነ ምግባር ብልሹነት የሚገልፅ ነው። ነገር ግን፣ ያ በቢላ የማይደፈረው የጉማሬ ቆዳ የፀሃይ ብርሃን ሲነካው ስለሚሰነጣጠቅ ቀን-ቀን ሙሉ አካሉን በውሃ መሸፈን አለበት። ማታ ላይ ደግሞ ሳርና ቅጣላ-ቅጠል ለመመገብ ይወጣና ሲነጋጋ ተመልሶ ወደ ውሃው ይገባል።*

*ለምሳሌ እኔ "በጠብታ ውሃ ውስጥ ጉማሬ አየሁ!" ብል ሊከተል የሚገባው ጥያቄ "ነገሩን ያየኸው ቀን ወይስ ማታ?" የሚል መሆን አለበት። በዚህ መልኩ፣ ማታ ላይ ዝናብ እየዘነበ ሳለ ጉማሬው ምግብ ፈለጋ ሲወጣ በዝናቡ ጠብታ ውስጥ ስላየሁት ያልኩት ትክክል ነው። ነገሩ የሆነው ቀን ላይ ከሆነ ግን ያልኩት ነገር ተዓማኒነት አይኖረውም። በመሆኑም፣ አንድ ጋዜጠኛ/ፀሃፊ እውነት ሲፅፍ እውነትነቱን ያረጋግጣል፣ ማህበረሰቡን ያሳውቃል። በተመሳሳይ፣ የፀፈው ውሸት ከሆነ አሁንም የነገሩን እውነትነት ከማረጋገጥ የዘለለ ሚና አይኖረውም። ምክንያቱም፣ የተፃፈው ነገር ውሸት ከሆነና ይህንን በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ ውድቅ የሚያደርግ ሌላ ፅሁፍ እንዲፃፍ ስለሚያደርግ፣ አንድ ጋዜጠኛ/ፀሃፊ ውሸት በመፃፉ እውነት እንዲታወቅ ያደርጋል፤ በዚህም ማህበረሰቡን ያሳውቃል።*

*ከዚያ ይልቅ፣ አንድ ጋዜጠኛ/ፀሃፊ የፃፈው ነገር ውሸትም ሆነ እውነት "ፀረ-ሰላም...ፀረ-ልማት...ከተለያዩ የአሸባሪ ድርጅቶች...ከፀረ-ሰላም ሃይሎች ጋር ግንኙነት........" ወዘተ በሚሉ ውንጀላዎች እስር-ቤት የምገባ ከሆነ፣ ከማንም የሚጎዳው "እውነት" ራሱ... እውነትን ማወቅ ያለበት "ህዝብ" እንደ ህዝብ፣ በእውነት ላይ ተመስርታ መመራት ያለባት "ሀገር" እንደ ሀገር...ሁሉም ይጎዳሉ። አሁን በእስር ቤት ያሉ ጋዜጠኞች፣ ፀሃፊዎች እና ጦማሪያ ይፈቱ የምንለው እንደ ህዝብና እንደ ሀገር ሁላችንም ስለምንጎዳ፣ ...እየተጎዳንም ስለሆነ ነው።*

## [ግጥም፡ ምን ፈረደባቸው?]

*ከእሱ በፊት ስሙ፣*
*ከሰው በፊት ብሔር*
*ከምግባር ይልቅ በዘር...*
*...ሃገስ፣ ቶላ፣ ኩራባቸው*
*እንደው ምን ፈረደባቸው?*
*የዘር ጥላቻ መድፊያ*
*የዘረኛ ዛቻ ማራገፊያ*
*ሲሆን መጠሪያ ስማቸው፣*
*በቁልምጫ የሚጠሩበት*
*ጥላቻ እና ዘረኝነት*
*እየተቆላ ታፈሰበት...*
******
*ታህሳስ፣ 2008 ዓ.ም*

## [July 19, 2015፡ ትግራይ: እማማ ብሬ'ን ወይስ ዘርዓይ'ን??]

*ትግራይ...መቀሌ...ዓዲ-ሃቂ ሰፈር...ትግራዋይቷ እማማ ብሬ ግቢ ሦስት ጓደኞቼ ቤት ተከራይተው ይኖራሉ። ከጎንደር፣ አምቦ እና ሰመራ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡና የማስተርስ ድግሪ ትምህርታቸውን በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ዓዲ-ሃቂ ካምፓስ የሚከታተሉ ናቸው። እነዚህን ሰዎች በአንድ ላይ ያገናኛቸው ከምንም በፊት ሰውነት (ሰብዓዊነት) ነው። በመቀጠል የአከራይና ተከራይ የጥቅም ግንኙነት። ለአሁን ዘመን ፖለቲካ እንዲያመች ደግሞ ከየትኛው ብሔር እንደመጡ ልንገራችሁ፤ ወላይታ፣ አማራ፣ ኦሮሞ እና ተጋሩ (ትግሬ) ናቸው። በቅድሚያ ግን ስለ እማማ ብሬ ትንሽ ልበላችሁ።*

*እማማ ብሬን በጣም እወዳቸዋለሁ። እድሜያቸውን ከ60 አመት በላይ ይመስለኛል። በእሳቸው አቆጣጠር ግን፣ እምናም፣ ዘንድሮም፣ በየአመቱ 53 ናቸው። አቤ...ት ደግሞ ውፍረታቸው! በጣም ወ...ፍራም ናቸው! በወጣትነታቸው ዘመን መቀሌ ከተማ ውስጥ የታወቀ ሆቴል ነበራቸው። "ዋህ...ያኔ'ኮ በቀን 30ና 40 አሩስቶ ብቻዬን እሰራ ነበር" ይሉኛል። ዛሬ እንዲህ በሦስት እግር እንዲንቀሳቀሱ ያደረጋቸው (ሦስተኛው እግር ከዘራ ነው)፣ በተለይ ታክሲ ውስጥ የሁለት ሰው ሂሳብ እንዲከፍሉ ያደረጋቸው ይህ ቅጥ-ያጣ ውፍረታቸው ከበግና ዶሮ አሩስቶ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። (...የታክሲው ነገር'ኮ በእውነት የሆነ ነው! እማማ ብሬ ጋቢና ከተሳፈሩ ከሹፌሩ በቀር ለሌላ ተሳፋሪ የሚሆን አንዲት ጋት ቦታ የለም። እሳቸው ጋቢና ከገቡ፣ እንኳን ሌላ ተሳፍሪ መጨመር ማርሽ መቀየር በራሱ መከራ ነው! የማርሹ እጀታ ከዳር-ዳር ከተዘረጋው የእማማ ብሬ ባት ስር በስንት መከራ ተፈልፍሎ ነው የሚገኘው። አንድ ቀን የታክሲ ረዳቱ "...ዓዲ-ሃቂ...ዓዲ-ሃቂ...ሁለት ሰው!" እያለ ነበር። ታዲያ እማማ ብሬ ባንዴ ጋቢናውን ሲሞሉት አይቶ "ዋይ...ናይ ክልተ ሰብ ትከፍልኺዲያ?" ብሎ የሁለት ሰው ሂሳብ አስከፈላቸው)*

*እኔ የእማማ ብሬ ግቢ ተከራይ አልነበርኩም። "ጓደኞቼ'ጋ ስሄድ ነው የወኳቸው። እርግጥ "ተው አንተ ረባሽ እብድ እኔ'ጋ ግባ?" እያሉ እሳቸው ግቢ እንድከራይ ለምነውኛል። የእሳቸው ግቢ የሚዘጋው ሦስት ሰዓት ላይ ነው። ለእኔ ደግሞ ምሽቱ ልክ በዚያን ሰዓት የሚጀምረው። ታዲያ ሁሌ ጓደኞቼ'ጋ ስሄድ "እሃሃሃሃ....ይሄ ረባሽ እብድ መጣ! አን..ተ! ና...ስቲ! ሰሞኑንማ አስቸግረሃል!" ይሉኛል። ለምን? ሃሃሃሃ.... ምሳ ሰዓት ላይ "ወጥ! ወጥ ያለው? ዜድ!...ነጋሳ!...ተሼ! በናታችሁ ወጥ ካላችሁ፣ ደረቅ እንጀራ ገዝቼያለሁ?" እያኩ ግቢውን ብጥብጥ ስለማደርግ፣ (በደሞዝ የምግብ ኮንትራት አይያዝም፣ ጨጓራውን የሚፈልግ ወጥ የምትሰራ ሰራተኛ አይቀጥርም። በተለይ ማስተርስ ላይ ሁሉም የአስተማሪ-ተማሪ ሁላ ደረቅ እንጀራ በፌስታል ገዝቶ፣ ወጥ በራሱ ሰርቶ ነው የሚማረው! እኔ ደግሞ ወጥ መስራት ኡህህ ሲያስጠላኝ!)*

*እማማ ብሬ "አንተ እብድ!...ና...ስቲ?" ሲሉኝ፣ "ሃ...ይ ማሚ...ከመይኪ! ፒስ ነው? ምንነው?" እያልኩ እሄዳለሁ። እዚያ ግቢ በሄድኩ ቁጥር የሚልኩኝ ነገር አይጠፋም። "አንተ እብድ እስኪ ገብሬ ሱቅ ደርሰህ'ና? ሎሚ ግዛልኝ? ...ና ካርድ ግዛልኝ!?..." ሲልኩኝ፣ ሲቆጡኝ፣ ሲያወሩኝ ደ...ስ ይለኛል። "ስማ! አንተ ረባሽ...አልታዘዝም ማለትህ ነው? ና...ስኪ ፍሬወይኒ'ጋ ደውልልኝ።.... አንተ ስልኳ ጠራች! ና..ስኪ ማን ነው የደወለው?ፍሬወይኒ ነች?" እማማ ብሬ ፊደል አልቆጠሩም። የሞባይል ቁጥር ለይተው አይደውሉም፣ የደወለውንም ሰው ለይተው ለያውቁም።*

*አዎ እማማ ብሬ አልተማሩም! በወጣትነታቸውን የዶሮና የበግ አሩስቶ እየሰሩ፣ አሁን ደግሞ በወጣትነታቸው ዘመን ባፈሩት ሀብት ባለ አንድ ፎቅ ቤት ሰርተው እሱን እያከራዩ ነው የኖሩት።*
*አዎ እማማ ብሬ፤ እንደ #ዘራይ_ሀይለማሪያም፣ እንደ #ጀዋር_መሀመድ፣ እንደ #ሴቭ_ሸዋ፣ ዘመናዊ ትምህርት የመማር እድል አልነበራቸውም። እርግጥ ነው እማማ ብሬ አልተማሩም፣ እንደነዚህ ሰዎች በዘረኝነት ልክፍት አላበዱም።*

*አዎ እማማ ብሬ የፈረንጅ ፊደል፣ የቅንጦት ቃል አልተማሩም። በዘረኝነት ጠበል አልተጠመቁም! እማማ ብሬ አልተማሩም፣ በድንቁርናቸው አይኮሩም! ስላልተማሩ ሁሌም የሆነ ነገር እንደቀራቸው ያስባሉ፣ በሰው ላይ በእርግጠኝነት ለመፈረጅ አይቸኩልም። እሳቸው እኔም ሆንኩ ሦስቱ ጓደኞቼ በቅድሚያ ሰዎች ነን።*

*እማማ ብሬ አልተማሩም፣ እንደነዚህ ግልገል ጭራቆች ከሰውነት በፊት ዘርና ሃይማኖትን አያስቀድሙም። እንደ እንስሳ የሰውን ማንነት በመንጋው ምንነት አይፈርጁም። እማማ ብሬ ዘመናዊ ትምህርት አልተማሩም፣ አልዘመኑም! አልሰለጠኑም! አልሰየጠኑም! እንደ ዘራይ፣ ጀዋርና ሴፍ ሸዋ የሰለጠኑ መስሏቸው አልሰየጠኑም። እንደነሱ "ሰው እርስ-በእርሱ እንዲጫረስ ትጉ" የሚል አጋንንት በእሳቸው ላይ አልሰፈረም።*

*ለእኔ "ትግራይ" ሲባል በቅድሚያ ወደ አዕምሮዬ የሚመጣው እማማ ብሬ እንጂ ዘርዓይ አይደለም። ምንም ቢሆን አንድ ማህብረሰብ በጤነኛ እንጂ በእብድ ሰው አይመሰልም!!!*
*******************************

*(ለዚህ ፁሁፍ መነሻ የሆነው በ"Tsegaye R Ararssa" እና "Zeray Halemariam መካከል ተደረገ የተባለው የመልዕክት ልውውጥ ነው። ውይይቱ በእውን የተደረገ ይሁን-አይሁን የፅሁፉ ሃሳብ በይፋ ተንፀባርቋል። ስለዚህ፣ "ዘርዓይ ሀይለማሪያም" የሚለው "Zeray Halemariam" የሚባለውን ግለሰብ ወይም የእሱን ስም ጠቅሶ ይህን የዘረኝነት ልፋጭ ያዝረከረከው ግለሰብን ብቻ የሚወክል ነው። ጃዋር መሀመድ እና ሴፍ ሸዋ ይህን የዘርነት ልፋጭ በይፋ ስለማዝረከረካቸው ግልፅ ነው።)*
*******************************

*ስዩም ተ.*

## *Aug 1, 2015፡ አየሽ...እኔ ኢትዮጲያዊ ነኝ።*

*የነፃነት ድልህ የተቀባ የድህነት ሕይወት እየላሰኩ ያደኩ። "መስከረም" የሚል የአብዮታዊ ደርግ መፅሄት ታውቂያለሽ። ከመማሪያ መፅሃፍት ውጪ መጀመሪያ ያነበብኩት መፅሄት ነው። ስወለድ ጀምሮ የማወቅ ሱስ የተጠናዎተኝ...የሃቅ መጋኛ የመታኝ መሰለኝ...እያንዳንዷን እውነት የመፈልፈል አመል ተጠናውቶኝ፣ ይሄው ስቆፍር...ስቆፍር...እውላለሁ። ስለ ምን እንደምቆፍር ታውቂያለሽ? ለምን የእኛ ኢትዮጲያኖች ሕይወት በማጣት ስቅታ ተጀምሮ በማጣት ስርቅርቅታ እንደሚያከትም ለማወቅ። ይህ እና ይህን ብቻ እየጠቁ አምስት አመት መኖር...ሕይወት ረስቶ አንድና አንድ ጥያቄ መኖር ታስቦሻል? ከዚያስ? ማንም መስማት የማይሻው እውነት ላይ መድረስ፣ አንቺ ምለሽ የተገዘትሸበት እምነት የዚቺ ሀገር እድገትና ብልፅግና ፀር እንደሆነ፣ ላመነ...በእምነቱ ለሚኮራ አማኝ፣ እምነቱ እንኳን ለስጋውም ሆነ ለህላዌው ካንሰር እንደሆነ ስታውቂ ምንና እንዴት ብለሽ...ምን፣ ለምንና እንዴት ማለት እንዳለብኝ ሳታስረጂኝ...ምንም አትበይኝ! ምንም እንዳትይኝ...ዝም ...ዝም በይኝ!!!*
*እውነት ለመቀበል ዝግጅ ሳትሆኝ አትጠይቂ። እኔን እጅህ ከምን እንዳትይኝ!!!*

## *Jul 13, 2015፡ አውቀው ኢያጠፉም-ከአጠፉም አላወቁም!*

*እኔ በራሴ ነፃ ፍላጎትና ምርጫ የመኖር መብት አለኝ። ይህ በነፃነት የመኖር መብት የእናንተን በነፃነት የመኖር መብት እንዳከብር ከተጣለብኝ ግዴታ ጋር እኩል ነው። ስለዚህ፣ ነፃነት የመብትና ግዴታን እኩሌታ ነው። ጌዴታዬን የምወጣው ግዴታህን እስከተወጣህ ድረስ ብቻ ነው። ግዴታቸውን ሳይወጡ "መብታችን ይከበር" የሚሉ ሰዎች መብታቸውን ነፍገ ግዴታቸውን እንዲወጡ ካስገደዳቸው ሌላኛው አካል ጋር አንድና ተመሳሳይ ናቸው። ያለበትን ግዴታ በአግባቡ የማይወጣ ማህብረሰብ መብቱን ጠንቅቆ አያውቅም። መብቱን የማያውቅ፣ ግዴታውን አይረዳም፣ ፍትህን አያውቅም፣ ፍትህን አይጠይቅም። በእንዲህ ያለ ማህብረሰበብ የሕግ የበላይነት ሊሰፍን አይችልም። የግለሰብን መብት ሲጥስና ሲደመስስ የሚውል ማህብረሰብ መብት፣ ነፃነት፣ ዴሞክራሲ፣...ወዘተ፣ አይገባውም። "ወያኔ ይጥፋ!" እያለ የሚፎክርን ወያኔ ቢያጠፋው ወይም ሊያጠፋቸው ሲል ቢያጠፉት፣ አጥፊዎች ተጠፋፉ። በዚህ አይነት በመጠፋፋት ውስጥ በዳይና ተበዳይ፣ መብትና ግዴታ፣ ፍትህና እኩልነት የለም።*

*የሌሎችን መብት እንዳይጥስ የተጣለበትን ግዴታ እየተወጣ ሌላውም እንደሱ እንዲያደርግ በምሳሌ የሚታገል ነው። እየሱስ ክርስቶስ፣ መሃተመ ገንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ እና ኔልሰን ማንዴላ፣ በዚህ የትግል ስልት ታግለው ያሸነፉና በዚህም ዘላለማዊ ክብር የተጎናፀፉ ናቸው። ነገር ግን፣ አንተ ያልሆንከውን ሌሎች እንዲሆኑ ስትጠይቅ እነሱምን እንደ አንተ እንዲሆኑ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ የለውም። በጠቅላላ ጉባኤ በአባላት ነፃና ገለልተኛ ምርጫ የተወከለ አመራር የሌለው የፖለቲካ ፓርቲ ምርጫ 2007 ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን ምን አይነት አስተዋፅዖ ሊያበረክት ይችላል?*

## *Feb 24/2016፡ ኣላዋቂ፡- ደጋፊዎች...ተቃዋሚዎች...ገዢዎች*

*እስኪ... ለመሰረተ-ልማት ግንባታ በሚል መንግስት የወላጆቻችሁን የእርሻ መሬት 20 ብር በካሬ ሜትር ካሣ እየከፈለ እስከመጭሻው ቢያፈናቅላቸው ምን ይሰማችኋል? ለነበራቸው ብቸኛ 1ሄክታር መሬት 200ሺህ ሲሰጣቸው በቂ የመሰላችሁ ካሣ ብር፣ ባልና ሚስትን ከአምስት ልጆቻቸው ጋር ከሦስት አመት በላይ ማኖር ሲሳነውና፤ እናት የሰው ቤት እንጀራ ጋጋሪ፣ ባል ዘበኛ ሆኖው ስታዩ ምን ዓይነት ስሜት ይፈጥርባችኋል? አዎ...ይሄን ፍፁም ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እንደሆነና ማንኛውም ሰው አጥብቆ ሊያወግዘው እንደሚገባ ይሰማችኋል:: በእርግጥ፣ በምታደርጉት የተቃውሞ እንቅስቃሴ አብሮ ከጎናችሁ እንዲሰለፍ፣ ያም ባይሆን የሞራል ድጋፉን ሊነፍጋችሁ እንደማይገባ ታምናላችሁ:: "ወላጅ-ዘመዶቼ ያለአግባብ ሊፈናቀሉ አይገባም!" እያላችሁ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ስትጀምሩ፣ ሌላው ሰው አብሯችሁ ባይሰለፍ፤ ስትታሰሩ፣ ስትደበደቡና ስትገደሉ "አይዟችሁ!" የማይል ከሆነ ሰብዓዊነት እንኳን የጎደለው እንደሆነ ይመስላችኋል::*

*እንደ የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ሁሉ፣ ባህር-ዳር፣ መቐለ፣ ጅማ፣ አሶሳ፣ ሃዋሳ፣ ....ሁሉም ከተሞች የራሳቸው-ሚኒ-ማስተር ፕላን አላቸው፡፡ የእኔዋ ወሊሶ እንኳን የራሷ ማስተር ፕላን አላት፡፡ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በሚዘጋጅ ማስተር ፕላን በከተማ ሥር በሚካተቱ የገጠር ቀበሌዎች ያሉ አርሶ-አደሮች ከ500 ካሬ ሜትር ውጪ ላለ መሬታቸው መንግስት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ካሣ እየከፈለ እያስነሳቸው ነው። ለምሳሌ፣ አሁን የምኖርበት ኮንድሚኒዬም እኔ ለመጀመሪያ ግዜ ወሊሶ ስመጣ ሰፊ የጤፍ እርሻ መሬት ነበረ፡፡ ሌላዋ በቅርብ የማውቃት የመቐለ ከተማ፣ ዓዲ-ሃቂና ዓዲ-ሃውሲ የሚባሉት ቦታዎች ብቻ ከተማዋ ከ1997 ዓ.ም በፊት አጠቃላይ ከነበራት የቦታ ሽፋን እኩል ሊሆኑ ምንም አልቀራቸው? በእነዚህ የቀድሞ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አርሶ-አደሮች የት ገቡ? “በሌላ ቦታ፣ በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደርስ ችግርና ግፍ ነው!” በሚል በቸልተኝነትና ምን-አገባኝ ስሜት ዝም ያለ ሰው ካለ፣ በእርግጥ እሱ #አላዋቂ_ደጋፊ ነው። ኣላዋቂነቱ የሌሎችን ችግር መረዳት አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን፣ ችግሩ በራሱ ደጃፍ፣ በራሱ ወዳጅ-ዘመዶች ላይ እደረሰ ያለና፣ ይህንን ማገናዘብ የተሳነው ስለሆነ ነው።*

*ሽያጮችን አስጨንቆና አማራጭ አሳጥቶ፣ የመኖር-ህልውናቸው የተመሰረተበትን መሬት በርካሽ ዋጋ የሚገዛ ሰው #ኣላዋቂ_ገዢ ነው። እንዲህ ያለ ሰው በእርግጥ ራስ ወዳድ ከመሆኑም በላይ ቁንፅል እይታ ያለው ድኩማን ነው። በሌሎች መቃብር ላይ ሃብትና ንብረት ለመሰብሰብ የሚሞክር ሰው፣ ግዜው ይረዝም ይሆናል እንጂ፣ ሌሎች በቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ራሱ መቀበሩ አይቀሬ ነው። ገዢውም ቢሆን በአንተ መቃብር ላይ የሚሰራው ቤት በቅርቡ ፈራሽ እንደሆነ አለማወቁ፣ ያው ዞሮ ዞሮ "ኣላዋቂ" ነው። በአንተ ውድቀት ላይ ስኬት የሚያሰላ ኣላዋቂ ውድቀቱን እንጂ ስኬትን አላቀደም፣ ሊያቅድም።*

*"ከእኔ ጎን አልተሰለፉም፣ ...እኔ ላይ በደል ሲፈፀም፣ ...ጭቆናን በመቃወሜ ብቻ ስታሰር፣ ስቆስል፣ ስገደል...ዳር ቆሞ ያየኝ ሁሉ ጠላቴ ነው" ብለህ ዘራፍ የምትል ደግሞ #ኣላዋቂ_ተቃዋሚ ነህ። የመቐለና ጎንደር ሰው አቋምኽን በይፋ ደግፎ ስላልወጣ ብቻ በጠላትነት እየፈረጅክ፣ አንዳንዴ በስድብ፣ ሌላ ግዜ በድንጋይ፣ ...ሲብስ በእሳት ስትጠብሰው፣ ... ፍርሃት እየዘራህ ጭቆናን ታጭዳለህ እንጂ ነፃነትን አትቀዳጅም። በትግል እያለህ ያስፈራራህው ጎረቤት፣ ነፃ ስትወጣ እንደምትበቀለው ያስባል፣ ይፈራሃል። ያንተ ነፃነት በምንም መልኩ ለጎረቤቶችህ ስጋት መሆን የለበትም። አየህ ወዳጄ... "ኣላዋቂው-ገዢ" ለገዛው መሬት የፈሩኽን የጎረቤት ልጆችን በዘበኛነት ቀጥሯል። ከዛም፣ የአንተ እንቅስቃሴ ከገዢው አልፎ በዘበኞቹ ሕልውና ላይ የመጣ አደጋ እንደሆነ ኣላዋቂ ነውና ይነግራቸዋል፣ ኣላዋቂ ናቸውና ያምኑታል። ኣላዋቂ ነህና ያንተ ነፃነት ለእነሱ ስጋት ይሆናል፣ እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ ይፋለሙሃል፣ ለነፃነት በምታደርገው ጉዞ ሁሉ እንቅፋት ይሆኑሃል።*

*ነፃነት፡- የኣላዋቂን ኣለማዋቅ አውቆ እሱን በማሳወቅ የሚመጣ  የድል ብስራት ነው። ለኣላዋቂነት የሚሰጥ ሽልማት አይደለም። በፍርሃትና ማስፈራራት ነፃነትን ከማሳካት ይልቅ የገዢውን እድሜና ውል ማራዘሚያ ነው።*

## [July 28,2015፡ ክፉ ሰው' ካለ 'ሰው' መሆን አልሻም!]

*"ሰው አውቆና ፈቅዶ በሌሎች ሰዎች ላይ ክፉ ነገር አይፈፅምም!" የሚል የሕይወት መርህ አለኝ። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በነፃነት (በነፃ ፍላጐትና ምርጫ) በሌሎች ሰዎች ላይ "ክፉ" ነገር አያደርግም። አንድ ሰው ከሕግም ሆነ ከሞራላዊ እሳቤ  አንፃር ጥፋተኛ ሊሆን የሚችለው በጥፋተኝነት ያስፈረጀውን ተግባር በነፃነት የፈፀመው ከሆነ ብቻ ነው። በነፃነት የተፈፀመ ተግባር ድርጊት-ፈፃሚው አውቆና ፈቅዶ ያደረገው ሲሆን ነው። ለመፍቀድ ማወቅ፣ ለማወቅ ደግሞ መፍቀድ አለበት። ሰው በራሱ ፍቃድ (by his own Free Will) ላደረገው ተግባር ተጠያቂ ይሆናል።*

*ከዚህ በተረፈ፣ ሰው በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለፈፀመው ተግባር ግን ተጠያቂ አይሆንም። ለምሳሌ፣ እንበልና አንዲት ሴት ከአንድ ሱቅ ዳቦ ሰረቀች፣ የሚያስፈልገውን ክፍያ ሳትፈፅም ዳቦውን ደብቃ ወሰደች። ስርቆት በሕግም ሆነ በሞራል ደረጃ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ነው። የሴትዮዋን ተግባር አግባብነት "ጥሩ" ወይም "መጥፎ" ብሎ ለመፈረጅ፣ ከቦታ፣ ግዜና ምክንያት አንፃር ያለን ግንዛቤ ወሳኝ ነው። ሴትዮዋ በዚያ ቦታና ግዜ የምትከፍለው ገንዘብ የሌላትና የ3ወር ልጇ ባዶ ጡቷን በድዱ ነክሶ እያለቀሰ ቢያስቸግራት፣ የልጇና የራሷ ሕይወት ቢያስጨንቃት፣ ህልውና (ህላዌ) ከምንም ይቀድማልና (Necessity has no law) ዳቦውን መስረቅ በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ የተደረገ ነው። ይህን ነባራዊ እውነታ ሙሉ-ለሙሉ ካልተገነዘብን ሴትዮዋ ስርቆቱን በራሷ ነፃ ፍላጐትና ምርጫ እንዳደረገችው፣ በዚህም በሌብነት መጠየቅ እንዳለባት ልንወስድ እንችላለን።*

*የአንድን ሰው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከቦታ፣ ግዜና ምክንያት አንፃር ሙሉ በሙሉ መገንዘብ ከቻልን ግን ተግባሩ በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እንደተፈፀመ እንረዳለን። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተደረገ ነገር በግዴታ እንጂ በፍላጐትና ምርጫ እንደተደረገ ተደርጐ ሊወሰድና ተጠያቂ ሊደረግ አይገባም።*

*አንድ ሰው አሁን እኔ ይሄን ፅሁፍ የምፅፍበትን ምክንያት፣ ቦታና ግዜ ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት የእኔን አመለካከት፣ እሳቤና አስተሳሰብ፣ በውስጤ እየተሰማኝ ያለውን ስሜት መረዳትና ዛሬ ያስተዋልኩት እውነታ ማስተዋል፣ እንዲሁም እኔ ያለሁበትን ቦታና ግዜ ማወቅ አለበት። ይህን ሙሉ ለሙሉ መረዳት የሚችለው በአካልና መንፈስ እኔን መሆን ከቻለ ብቻ ነው። እኔን መሆን ከቻለ ደግሞ አሁን የማደርገው ያደርግ ነበር።*

*ይህ እንደሌሎች የተፈጥሮ ሕጎች የማይነቃነቅ ቋሚ የሆነ የሰው-ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። አንድን ሰው 'ከዚህ ተፈጥሯዊ ባህሪ ውጪ ነው' የምትሉኝ ከሆነ "በእርግጥ እሱ ሲጀመር  *ሰው* ነው'ን?" ስል እሞግታችኋለሁ። "አውቆና ፈቅዶ በሌሎች ሰዎች ላይ ክፉትን የሚያስብና የሚሰራ ሰው አለ" ብላችሁ ካሳመናችሁኝ ግን "ሰው" የሚለውን የክብር ስያሜ ከእኔነቴ ይገፈፍ እላለሁ። ያኔ ከሕይወት ይልቅ ሞትን እመርጣለሁ!!!*

### *ክፉ ሰው ካለ ሰው መሆን አልሻም።*

*******

*ሰዩም ተ.*

*******

*በመጨረሻም*

*እኔ እንኳን “ዘረኛ”ልሆን ቀርቶ ክፋት ማሰብ አልወድም...ጥላቻን ኣላስብም...ለክፋት የሚሆን ህሊና የለኝም። እኔ ጥላቻና ቂምን የሚሰብክ ስብዕና የለኝም። ይህ እኔ በእውን የሆንኩት ነው። እናንተ ደግሞ ወይ የሆንኩት አሊያም የመሰላችሁትን ማሰብ፣ ማለትና መውሰድ ትችላላችሁ። ለምትሰጡኝ ሃሳብና አስተያየት በቅድሚያ አመሰግናለሁ።*